## ይኸንም ቀድሜያለሁ

### ቁም ነገር በምሳሌያዊ ግጥም ከነቅዓ ጥበብ

ዱሮ ቀደም ብሎ፣ አገር ቤት እያለሁ፣
አስገራሚ ነገር፣ ተረት ሰምቻለሁ፣
የትኛውም ቦታ፣ ቤተስኪያን ባለበት፣
እንደሚታወቀው፣ እሁድ እሁድ ዕለት፣
ቅዳሴ ሲፈፀም፣ በዕለተ-ሰንበት፤
እማማ ትልቋ፣ ቤት ለቤት ዟዙረው፣
“ስለምንተ-ሰንበት!”፣ ተዘከሩኝ ብለው፣
ያገኙትን ዱቄት፣ በስልቻ ቋጥረው፣
የሰንበትን ፃዲቅ፣ ወይም  ነባብሮ፣
ጋግረው፣ ተሸክመው፣ በቤተስኪያን ጓሮ፣
ያስቀምጡትና፣ ቅዳሴ ሲወጣ፣
ለባራኪው ካህን፣ የሰንበቱን ቂጣ፣
ያቀርቡለትና፣ ባርኮና ፈትቶ፣
ቤተስኪያን ለመጣ፣ በእምነቱ ፀንቶ።
እማሆይ ለሁሉም፣ “ስለሰንበት” ብለው፣
የተፈተተውን፣ አድለው አድለው፣
ምዕመናን ተሳትፈው፣ ካህኑ ባርኳቸው፣
ይሰናበታሉ፣ ወደዬ ቤታቸው።
ታዲያ ባንድ ሰንበት፣ ሁሉን ያስደመመ፣
ያልታሰበ ነገር፣ ትንግርት ተፈፀመ።
እንደተለመደው፣ ቅዳሴ ሲያበቃ፣
በአውደ-ምህረቱ፣ ምዕመኑ ሲንቃቃ፣
ባራኪው መጡና፣ እንደ ዱሮው ሁሉ፣
እማሆይን ጠርተው፣ “ፃዲቁን ያምጡ!” አሉ፣
ለካስ እማሆይም፣ አመም አድርጓቸው፣
የሰንበቱን ዱቄት፣ ሳይለምኑ ቀርተው፣
አንድ ነባብሮ፣ ብቻ ጋግረው ኑሮ፣
ያንኑ አቀረቡ፣ እያሰሙ እሮሮ።
ቄሱም ባረኩና፣ ያንኑ አንድ ፃዲቅ፣
ከሶስት ቦታ ቆርሰው፣ ሳይሰነጣጠቅ፣
“አንድ እጅ ለባራኪ፣ አንድ እጅ ለቀዳሽ”፣
ብለው  ወሰዱና፣ ሁለቱንም ቁራሽ፣
የቀረውን ደግሞ፣ “የቀደም ይውሰድ”
ብለው ሲናገሩ፣ አንዱ ምዕመን ቢሄድ፣
“ይህንንም ቢሆን፣ እኔ ቀድሜያለሁ፣
እግዜር ይባርካችሁ፣
ይኸው ጨርሻለሁ፣
ፈትት ለሕዝብከ፣ ገምድል ለርዕስከ፣
በሚለው መሰረት፣ አከናውኛለሁ!”

አሉ እየተባለ፣ ሲነገር ሰምቼ፣
ሲገርመኝ ይኖራል፣ ስሙኝ ወገኖቼ።”
ዘንድሮም በምርጫው፣ መምሬ መለስ፣
አንዱን ቂጣ ከሶስት፣ በመቆራረስ፣
ለ (ወያኔ፣ ብአዴን፣ ኦሕዴድ ስሉስ)፣
ሁሉንም ወሰደው፣ ምንም ሳያቀምስ፣
እንዲህ ያለ ፈታች (ባራኪ)፣ አይጣል! አያድርስ!
በጣም አሳዘኑኝ፣ እማሆይ ኢትዮጵያ፣
ትርፍ የሌለው ድካም፣ የሌባ ገበያ!